# በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ፌድሬሽን

## የ ኢትዮ - አሮፕ 2008 እግር ካስ ውድድር መመሪያ

### አገስት 1 እና 2  2008 ስቶኮልም ፤

1. የእያንዳንዱ ቡድን ሃላፊ ውድድሩ ከመጀመሩ በፊት የቡድኑን ተጨዋቶች ስም ዝርዝር እስከ 25 ሰው ለውድድሩ በተዘጋጀው ፎርም ሞልቶ ለቴክኒክ ዘርፉ መስጠት አለበት።
2. የእያንዳንዱ ቡድን ሃላፊዎች፣ ተጨዋቶችና የቡድን መሪዎች ለሚያደርጉት ህገ - ወጥ ተግባሮች በህግ ተጠያቂዎች ናቸው።
3. የእግር ካስ ውድድር አካሄድ የፊፋን ህጎችን በመከተል ተግባራዊ ያደርጋል።
4. የእያንዳንዱ ቡድን በአንድ ጨዋታ እስከ አራት(4) ተጨዋቶች መቀየር ይችላል። በአንድ ጊዜ ከአራት በላይ ተጨዋቶች ቀይሮ ቢገኝ ግን በጨዋታው ተሸናፊ ይሆናል።
5. አመታዊ የአባልነት መዋጮ ያልከፈለና ገቢ ያላደረገ ቡድን ውድድሩን አይካፈልም።
6. አንድ ተጨዋች ከውድድሩ በፊት ለተመዘገበበት ቡድን ብቻ መጫወት ይችላል። ለሌላ ቡድን ሲጫወት ቢገኝ፣ ቡድኑ በሁለት ለባዶ ተሸናፊ ይሆናል።
7. በፕሮግራሙ መሰረት በጨዋታው ሜዳ ላይ ከተባለው ጊዜ እስከ አምስት ደቂቃ ለጨዋታ ተዘጋጅቶ ያልቀረበ ቡድን በሁለት ለባዶ ተሸናፊ ይሆናል። በተጨማሪም ቡድኑም በፌድሬሽኑ ጨዋታው-ን ባለማካሄዱ ይቀጣል።
8. ጉልበትን ወይም ሀይልን በመጠቀም ሌላውን ሰው አውቆ ለመጉዳት የሞከረ ወይም የፈፀመ ተጨዋች፣ ሃላፊና አሰልጣኝ ከማንኛውም ስፖርታዊና ባህላዊ ዝግጅት ውስጥ በተጨዋችነትም ሆነ በሃላፊነት የመካፈል መብት የለውም። እንደ ሁኔታውም ታይቶ በህግ ፊት ቀርቦ እንዲዳኝ ይደረጋል።
9. ጨዋታውን አስመልክቶ የአጨዋቱን ዳኛ ውሳኔ የመጨረ ሻ ው ስለሆነ፣ ምንም አይነት ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም።
10. ቢጫና ቀይ በማግኘት ከጨዋታው ሜዳ እንዲወጣ የተደረገ ተጨዋች አንድ ጨዋታ ሲቀጣ፣ ቀይ ካርድ በማግኘት ከሜዳ የወጣ ተጨዋች በተከታታይ ሶስት ጨዋታዎች ይቀጣል። ነገር ግን የተቀጣ ተጨዋችን አሰልፎ የተገኘ ቡድን ቢኖር፣ ቡድኑ በውድድሩ ተሸናፊ ይሆናል።
11. የአውሮፓ የኢትዮጵያውያን የስፖርትና ባህል ፌድሬሽን በውድድሩ ተካፋዮች ላይ ሊሚደርሱ ጉዳትና የንብረት ጥፋት ሃላፊነት አይወስድም። እያንዳንዱ የውድድሩ ተካፋይ ቡድንና ሀገር ለራሱ ተጨዋቶች ዋስትና ሃላፊነቱን ይወስዳል።
12. አደንዛዥ እፆችን ይዞ ውድድሩ ቦታ መግባት የተከለከለ ስለሆነ፣ ይህንን ሲያደርግ የተገኘ ግለሰብ አዘጋጅ ሀገሩ እንደ አስፈላጊነቱ እርምጃ ይወሰዳል። ከአዘጋጅ ክፍሉ ፈቃድ ውጪ የሚደረጉ የሽያጭ እንቅስቃሴዎች የተከለከሉ ናቸው።
13. እያንዳንዱ ጨዋታ በአንድ አጨዋች ዳኛ እና በሁለት ረዳት ዳኞች ይመራል።
14. በማጣሪያው ውድድር ከየግሩፑ ከፍተኛውን ነጥብ ያገኘ ቡድን የግሩፑ አሸናፊ ሲሆን፣ ሁለት ቡድኖች በነጥብ እኩል ከሆኑ፣ በጎል ብልጫ ይወሰናል። በጎልም እኩል ከሆኑ፣ ብዙ ጎል ያገባው ቡድን አሸናፊ ይሆናል። ያገቡት ጎል ብዛት እኩል ከሆነ፣ የፍፁም ቅጣት ምት አሸናፊ የሆነው ቡድን አሸናፊ ይሆናል።
15. ከየግሩፑ 1ኛ እና 2ኛ የሆኑት ቡድኖች ለሚቀጥለው ውድድር ሲያልፉ ፣ ከየግሩፑ ሶስተኛ ከወጡት ቡድኖች መካከል ሁለት በጎልና በነጥብ ብዛት ከሌሎች በልጠው የሚገኙ ቡድኖች ለሚቀጥለው ውድድር በተጨማሪ ያልፋሉ። ከሁለቱ አንድ በነጥብና በጎል የተሸለው የግሩፕ 4 አንደኛ ሲሆን ፣ የተቀረው ሁለተኛ ይሆናል።
16. በውድድሩ ላይ ለአንድ ኮከብ በረኛ፣ ለአንድ ኮከብ ተጨዋች፣ ለአንድ ከፍተኛ ጎል ላገባ ተጨዋች እና በስፖርታዊ ጨዋነት ከፍተኛውን ነጥብ ማለትም አነስተኛ ካርድ ላገኘ ቡድን የተለያዩ ሽልማቶች ይሰጣሉ። 1ኛ፣ 2 ኛ ፣ 3ኛ የሆኑት ቡድኖች የዋንጫና የሜዳሊያ ሽልማት ይደረግላቸዋል። የሜዳሊያ ሽልማቱ ለእያንዳንዱ ቡድን ለ25 ሰዎች የሚደረግ ይሆናል።
17. የውድድሩ ኮከብ በረኛ እና ኮከብ ተጨዋች በተሳታፊ ቡድን አሰልጣኞች ይመረጣሉ። እነዚህም ለዋንጫ ከደረሱ ቡድኖች መካከል ይሆናል።
18. ዳኞች የትኛው ተጨዋች ከየትኛው ቡድን ቢጫ፣ ቢጫና ቀይ እንዲሁም ቀይ ካርድ እንዳገኘ ፣ የጨዋታውን ውጤትና የጎል አግቢ ስም ወይም አልባሳት ቁጥር በመጥቀስ ለውድድሩ አመራር ክፍል በያንዳንዱ ጨዋታ ያስመዘግባል።
19. የስፖርታዊ ጨዋነት ተሸላሚ የሚሆነው ቡድን በጠቅላላ ውድድሩ ወቅት ቡድኑ በአያንዳንዱ ጨዋታ ከዳ ኞ ች ቢጫ፣ ቢጫና ቀይ፣ እንዲሁም ቀይ ካርድ ብዛት ተደምረው ለቢጫ ካርድ 1፣ ለቢጫና ቀይ ካርድ 3፣ እና ለቀይ ካርድ 5 ነጥብ በመስጠት ከተባዙ በኋላ፣ አነስተኛውን ነጥብ ያስገኘ ቡድን አሸናፊ ይሆናል። ሁለቱም ቡድኖች እኩል ነጥብ ቢያገኙ በዕጣ ተሸላሚ ይሆናል።
20. ለሶስተኛነት ቦታ የሚደረገው ጨዋታ በተለያዩ ምክንያቶች ባይደረግ ፣ ለሶስተኛነት ከሚወዳደሩት ሁለት ቡድኖች መካከል በፍፁም ቅጣት ምት ከዚህ በፊት በነበረው ጨዋታ ያለ ፍፁም ቅጣት ምት ከተሸነፈው ቡድን ቅድሚያ ይኖረዋል። ስለሆነም ይህ ቡድን ሶስተኛ ይሆናል። ሁለቱም በፍፁም ቅጣት ምት የተሸነፉ ከሆነ ፣ በዕጣ ሶስተኛው ይወሰናል።

# በአውሮፖ የኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ፌድሬሽን

## ኢትዮ - አሮፕ ኦገስት 2008 ስቶኮልም፣ ስዊድን

*የቡድን ተጨዋቶችና ሃላፊዎች መመዝገቢያ*

**የቡድን ስም፤** ______________________________

| ቁጥር | ስም | የአባት ስም | መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |
| 6 | | | |
| 7 | | | |
| 8 | | | |
| 9 | | | |
| 10 | | | |
| 11 | | | |
| 12 | | | |
| 13 | | | |
| 14 | | | |
| 15 | | | |
| 16 | | | |
| 17 | | | |
| 18 | | | |
| 19 | | | |
| 20 | | | |
| 21 | | | |
| 22 | | | |
| 23 | | | |
| 24 | | | |
| 25 | | | |

**ከላይ የተመዘገቡት ተጨዋቶችና የቡድን ሃላፊዎች የቡድናችን ተጨዋቶችና ሃላፊዎች መሆናችንን በፊርማችን እናረጋግጣለን።**

**የቡድን ሃላፊ ሙሉ ስምና ፊርማ** ______________________________

**የቡድን አሰልጣኝ ሙሉ ስምና ፊርማ** ______________________________

# 6ኛው የአውሮፓ ኢትዮጵያውያን ስፖርትና በዓል ዝግጅት

## ዓመታዊ ውድድር ፕሮግራም

### ኦ ገስት 1 እና 2 ቀን 2008 ስቶኮልም ፣ ስዊድን፤

## <u>የአርብና ቅዳሜ ፕሮግራም</u>

## <u>አርብ</u>

| | |
|---|---|
| 09:00 - 09:30 | የተሳታፊ ቡድኖች መለያቸውን በማድረግ በሜዳው ላይ በተዘጋጀላቸው ቦታ ይሰለፋሉ።<br>የእንካን ደህና መጣችሁ አጭር የመክፈቻ ንግግር ከፌድሬሽኑ ተወካይ፣ ዕለቱ የክብር እንግዳና ከአዘጋጅ ሀገር ይቀርባል።<br>የቡድኖች ፎቶ መነሳና መተዋወቂያ ይሆናል። |
| 09:30 - 10:00 | ተሳታፊ ቡድኖች የተጨዋቶቻቸውን መታወቂያና ከቴክኒክ ኮሚቴ የተዘጋጀውን የመመዝገቢያ ፎርም በመሙላት ለቴክኒክ ኮሚቴው ያስረክባሉ።<br>የሜዳ ድልድል ዕጣ ይወጣል።<br>ተሳታፊ ቡድኖች የመልበሸ ክፍላቸውን እንዲያውቁና እንዲዘጋጁ ይደረጋል። |
| 10:00 | የመክፈቻ ጨዋታዎች በአራቱም ሜዳዎች ላይ ይጀመራሉ። |
| 10:00 - 18:00 | ለውድድሩ በቀረበው ፕሮግራም መሰረት ውድድሩ ተግባራዊ ይሆናል።<br>የሴቶች መረብ ካስ ጨዋታ ይደረጋል።<br>የመዝናና ዝግጅት ይካሄዳል። |
| 19: 00 | የእለቱ ፕሮግራም ፍፃሜ ይሆናል። |

## <u>ቅዳሜ</u>

| | |
|---|---|
| 10:00 | የሩብ ፍፃሜ ውድድሮች በአራቱም ሜዳዎች ላይ ይደረጋል። |
| 10:00 - 17:00 | ለውድድሩ በቀረበው ፕሮግራም መሰረት ውድድሩ ተግባራዊ ይሆናል።<br>የመዝናና ዝግጅት ይካሄዳል።<br>የመዝጊያ ንግግር ከፌድሬሽኑ ተወካይ ይደረጋል።<br>የሽልማት አሰጣጥ ፕሮግራም ይሆናል<br>የስፖርት በአል ፍፃሜ ይሆናል። |

## <u>ታላቅ የሙዚቃ ምሽት( ቅዳሜ ማታ)</u>

| | |
|---|---|
| 22:00 - 05:00 | ለዚሁ ምሽት በተዘጋጁት እውቅ ኢትዮጵያውያን የኪነት ባለሙያዎች ስፖርት አፍቃሪዎችን የሚያዝናኑበት ወቅት ይሆናል። |

# በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ፌድሬሽን

## Ethiopian Sport & Culture Federation in Europe( ESCFE)

ቀን :11/07/2008

ቁጥር: 010/ESCFE/2008

## ኢትዮ - ኢሮፕ ኦ ገስት 2008 የእግር ካስ ውድድር ተሳታፊ ቡድኖች በሙሉ፤

እንደሚታወቀው ሁሉ 6ኛው በአውሮፓ የአትዮጵያውያን ስፖርትና ባህል ቀን በስዊድን ሀገር፣ በስቶኮልም ከተማ ኦገስት 1 እና 2 ተከብሮ ይውላል። በዚህም ውድድር ላይ 20 ቡድኖች እንደሚሳተፉ የተረጋገጠ ሲሆን እነዚህም ተሳታፊዎች በአራት ምድብ ተከፍለው ውድድራቸውን ያካሂዳሉ።

ዝርዝሩንም በተመለከተ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የእግር ካስ ውድድሩን ጠቅላላ ፕሮግራም ድልድል፣ የእግር ካስ ውድድር መመሪያዎች ቅጽ 1 ፣ የቡድን ተጨዋቶች ሃላፊዎች መመዝገቢያ ቅጽ 2 እና የአርብና ቅዳሜ ፕሮግራም የላክን መሆናችንን በትህትና እንገልፃለን።

እያንዳንዱ ቡድን የተጨዋቶች መታወቂያ ካርድ ከእያንዳንዱ ተጨዋች ፎቶግራፍ ጋር በተለመደው መልክ አዘጋጅቶ መቅረብ ግዴታው መሆኑን አውቆ ይዞ እንዲመጣ እያሳሰብን በተጨማሪ እያንዳንዱ ቡድን በፌድሬሽኑ መተዳደሪያ ደንብና በቴክኒክ ዘርፉ ውስጠ ደንብ መሰረት አስፈላጊው የሆኑትን ቅድመ - ሁኔታዎች ሁሉ ሟሟላት ይጠበቅበታል።
ከዚህም ጋር በማያያዝ ቡድኖች ሁሉ የ 2008 የአባልነት ክፍያና የቀረ ውዝፍ( ያልተከፈለ) ክፍያችሁን ከውድድሩ መጀመር በፊት ገቢ እንድታደርጉ ፌድሬሽኑ በጥብቅ ያሳስባል።

በመጨረሻም ፌድሬሽኑ ይህ ከፊታችን የሚጠብቀን በአል የተሳካ እንዲሆን የሁላችንም ጥረት እንዲታከልበትና ሃላፊነታችን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ እንደሚሆን በመተማመን እስከዛው ድረስ ግን መልካም ምኞትና መልካም መንገድ እንዲሆንላችሁ ይመኝላችኋል።

ከማክበር ሰላምታ ጋር፣
የቴክኒክ ዘርፍ

አባሪ:-
የእግር ካስ ውድድር ጠቅላላ ፕሮግራም፣
የእግር ካስ ውድድር መመሪያዎች ቅጽ 1፣
የቡድን ሃላፊዎችና ተጨዋቶች መመዝገቢያ ቅጽ 2፣
የአርብና ቅዳሜ ፕሮግራም፣


ESCFE: Yohannes Messele, 71B Lonsdale Road, London W11 2DF
Telephone: 00442072211687 / Mobile: 00447932068838
Email: yohannes@hotmail.co.uk